# አቡነ መቃሪዮስ ሕዝብ ክርስትያኑ ራሱንና ቤተክርስትያኑን ከሰርጎ-ገቦች እንዲጠብቅ አስገነዘቡ

በአውስትራሊያ  የስራ ጉብኝት እያደረጉ ያሉት ብጹዕ አቡነ መቃርዮስ ሕዝበ ክርስቲያኑ ራሱንና ቤተክርስትያኑን ከሰርጎ-ገቦች እንዲጠብቅ አስገነዘቡ፡፡

ብጹዕ አቡነ መልከጼዴቅ የህጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሀፊና ብጹዕ አቡነ መቃርዮስ የካናዳ፣ አውሮፓ፣ አፍሪካና አውስትራሊያ ሊቀ-ጳጳስ በተገኙበት ኢትዮጵያዊያን በብዛት በሚገኙባቸው የአውስትራሊያ ዋና ዋና ከተሞች የ2012 የጥምቀት በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

ከጃንዋሪ 10 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በመላው አውስትራሊያ የተራዘመ የስራ ጉብኝት በማድረግ ላይ ያሉት ብጹዕ አቡነ መቃርዮስ በስደተኛዋ ቤተክርስትያናችንና በአገራችን ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ከሕዝበ ክርስትያኑ ጋር እየተወያዩ ናቸው፡፡ ብጹዕነታቸው በሜልበርን፣ ፐርዝ፣ ሲድኒ፣ ብሪዝቤን እና አደላይድ ከተሞች በመዘዋወር ሕዝበ ክርስትያኑ ራሱንና ቤተክርስትያኑን ከአስመሳይና ሰርጎ-ገብ “ካህናት” እንዲጠብቅ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

በስደት የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ክርስቲያኖች ክህነትና ምንኩስና ሳይኖራቸው በህዝበ ክርስትያኑ መካከል ሰርገው በመግባት በአንድነታቸው ጸንተው ለቤተክርስትያናቸውና ለአገራቸው እንዳይቆሙ እየከፋፈሏቸው ካሉት ተላላኪዎች እንዲጠነቀቁ ብጹዕነታቸው አስገንዝበዋል፡፡ ዛሬ አገራችን በከባድ ችግር ውስጥ በምትገኝበት ወቅት በውጭ የሚኖረው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ በአንድነቱ ጸንቶ ፈጣሪን መለመን ባለበት ሰዓት በሰርጎ-ገብ ሀሳዊ “ክርስትያኖች” ተንኮል ተጠልፎ ለቤተክርስትያን እድገትና በአገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ መስፈን እንዳይሰራ ሁኗል ብለዋል፡፡

ብጹዕነታቸው ለስራ በተዘዋወሩባቸው አንዳንድ የአውስትራሊያ ከተሞች በስደት የምትገኘዋ ቤተክርስትያን  በውስጥ ችግር እየታመሰች ህዝበ ክርስትያኑም ግራ እንዲጋባና በአንድነቱ እንዳይጸና ለማድረግ ሰውር ተንኮል አንግበው በውስጧ የተሰገሰጉ አስመሳይ “ክርስትያኖች” የሚያደርጉት የመከፋፈል ስራ መኖሩን እንደተገነዘቡና ህዝበ ክርስትያኑ ነቅቶ ቤተክርስትያኑን እንዲጠብቅና በአንድነቱ ጸንቶ ለአገሩ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰራ አባታዊ ምክራቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ብጹዕነታቸው ቤተክርስትያን መተዳደር ያለባት በህግ መሰረት ስለሆነ በአስተዳደር ጉዳይ የሚነሱ ችግሮች በሙሉ ህግን መሰረት አድርገውና በአባላቱ መንፈሳዊ ውይይት በሚሰጡ ውሳኔዎች መሆን እንዳለበት፤ እንዲሁም የክህነት ጉዳዮች በፍትህ ወ-መንፈሳዊ መሰረት በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የሚሰጥባቸው መሆናቸውን ጨምረው አስገንዝበዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ማናቸውም አይነት ችግር ቢፈጠር ህዝበ ክርስትያኑ በእምነቱና በአንድነቱ ጸንቶ የቤተክርስትያንን አንድነት ለመጠበቅ መቆም አለበት ብለዋል፡፡

በስደት የምትገኘዋን ቤተ-ክርስትያንንና ኢትዮጵያዊኑን ለመከፋፈል ለተመደቡ ሰርጎ-ገቦች ምንም አይነት በር ላለመክፈት ህዝበ-ክርስትያኑ ጥንቃቄ እንዲያደርግና እግዚአብሄር አገራችንን ካለችበት ችግር እንዲታደጋት አንድ ሁነን በጸሎት እንድንተጋ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ዛሬ በአገር ቤት ያለው ወገናችን ንብረቱን እየተቀማና የአገራችን የተፈጥሮ ሀብት ከዜጋው እየተነፈገ ለባእዳን እየታደለ ባለበት ሰዓት በውጭ የሚኖረው ክርስትያን ስደተኛ እርስ በእርሱ ከሚከፋፍለው ነገር ነቅቶና ራሱን ጠብቆ የአገራችን ህዝብ ለሚያደርገው የሞት ሽረት ትግል ድጋፉን እንዲሰጥ ብጹዕነታቸው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ብጹዕነታቸው በአሁኑ ሰዓት በምእራብ አውስትራሊያ ፐርዝ ከተማ የሚገኙ ሲሆን በፐርዝ ደብረ መድሀኒት መድሃኒያለም ወ-አርሴማ ቤተ-ክርስቲያን ከሰሜን አሜሪካ የተጋበዙ ዘማሪያንና ሰባኪያን የሚገኙበት መንፈሳዊ ጉባዔ ከፌብሯሪ 10-12 አርብ፣ ቅዳሜና እሁድ ለሦስት ቀን እንደሚደረግና ፌብሯሪ 12 እሁድ ከፐርዝ ደብረ መድሀኒት መድሃኒያለም   ወ-አርሴማ ቤተ-ክርስቲያን አባላት ጋር በቤተክርስትያን የአስተዳደር ችግሮች ላይና አዲስ ቤተ ክርስትያን ስለሚገዛበት ሁኔታ ተወያይተው መፍትሄ እንደሚሰጡ በወጣው ፕሮግራም ላይ ተዘግቧል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአደላይድ ደብረ ምህረት ቅዱስ ዑራኤል ቤተ-ክርስትያን አዲሱ የቤተ ክርስትያን ህንጻ ብጹዕ አቡነ መቃሪዮስ በተገኙበት  ፌብሯሪ 18፣ 2012 ተመርቆ ቅዳሴ ቤቱ ይከበራል፡፡ እንደዚሁም የሜልበርን ደብረ ሰላም መድሀኒያለም አዲሱ የህንጻ ዲዛይን በከተማው መስተዳድር ጸድቆ ስለተፈቀደ ስራው በቅርቡ እንደሚጀመር ብፅዑነታቸው አብስረዋል፡፡

ብፅዑነታቸው በአውስትራሊያ ያሉ ቤተ-ክርስትያናት የራሳቸው ዘመናዊ የቤተ ክርስትያን ህንጻ ባለቤት እንዲሆኑ ለማድረግ ህዝበ ክርስትያኑ እያደረገው ያለውን ጥረትም አመስግነዋል፡፡

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
February 10, 2012